# ያማረ ፍሬ ሁሉ አይበላም!

ኢብሳ ነመራ 02-23-17

መብትና ነፃነት ሲኖሩበት ዋጋው ይዘነጋል። መብትና ነጻነት ምን ያህል ውድ እንደሆነ የሚታወቀው ሲታጣ ነው። እድሜያችን ከ40ዎቹ አጋማሽ በላይ የሆንን ኢትዮጵያውያን ከአዲሱ ትውልድ በተለየ ሁኔታ የመብትና የነጻነትን ዋጋ እናውቃለን። ዋጋውን የምናውቀው ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊገደቡ የሚችሉትን ያህል በተገደቡበት በወታደራዊው ደርግ የመንግስት ስርአት ውስጥ ስላለፍን ነው። በወታደራዊው ደርግ የስልጣን ዘመን በዘውዳዊው ስርአት ጭምር ዜጎች *ትክክል ነው* ብለው ያመኑበትን አመለካከት በይፋ ማራመድ አይችሉም። ስርአቶቹ ከሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም የተለየ ማንኛውንም አመለካከት መያዝ፣ ማራመድ፣ በማንኛውም መንገድ መግለጽ፣ መከተል . . . እስከሞት የደረሰ ቅጣት ያስቀጣል። ይህ የተደረገው በሰላማዊ መንገድ መሆን አለመሆኑ ልዩነት የለውም። የአመለካካት ነጻነት ስላልተከበረ የዚህ ነጸብራቅ የሆነው የፕሬስ ነጻነትም በህግ ታግዶ ነበር። በተለይ በወታደራዊው ደርግ የስልጣን ዘመን ሃሳብን መግለጽ በቻ ሳይሆን ሌሎች የገለጹትን ሃሳብ በማንኛውም መንገድ ማዳመጥ፣ ማንበብ ያስቀጣ ነበር።

እድሜያቸው በሃያዎቹና በሰላሳዎቹ ክልል ያሉ የአዲሱ ትውልድ አባላት ኢትዮጵያዊያን ስላለፉ ስርአቶች ብትነግሩዋቸው ለማመን እንደሚቸገሩ ልብ በሉ። ምክንያቱም ዜጎች ያመኑበትን አመለካከት ሲከተሉ፣ ሲገልጹ፣ በፖለቲካ ፓርቲ ተደራጅተው አመለካከታቸውን ሲያራምዱ፣ መንግስትንና ገዢውን ፓርቲ ያለምንም ገደብ በይፋ ሲቃወሙ፣ አቋማቸውን እያሳወቁ፣ *እኔ እሻል እኔ* በሚል እየተከራከሩ ለፖለቲካ ስልጣን ሲፎካከሩ፣ በህዝብ ድምጽ ባገኙት ውክልና ልክ ስልጣን ሲጋሩ ወዘተ. ስላዩ ነው ለማመን የሚቸገሩት፤ የሰዎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነጻነቶች ሊጣሱ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ቢያውቁም፣ *በእጅ ያለ ወርቅ* ሆኖ የጎለማሶች ኢትዮጵያውያንን ያህል አያሳሳቸውም። የማይገሰስ፣ የነበረ፣ ያለና ለወደፊትም የሚኖር አድርገው የወሰዱበት ሁኔታ አለ። እርግጥ ያለፈውን ስርአት ከሚያውቁትም መካከል፣ አሁን በእጃቸው ያለ መብትና ነጻነት በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች የህይወት መስዋዕትነት የተገኘ መሆኑን የዘነጉበት ሲዘነጉ ይስተዋላል። *ታሞ የተነሳ እግዚሩን ረሳ!* እንዲሉ፤

ያለፉት ስርአቶች ታሪክ ሆነው ቀርተዋል። ለዚህ ያበቃቸው የአመለካከትና የብሄራዊ ማንነት ብዝሃነት ባለባት አገር አንድ አመለካከት (ርዕዮተ ዓለም) እና አንድ ማንነት የበላይነት እንዲኖረው ለማድረግ በመሞከራቸው ነው። ስርአቶቹ ኢ.ዴሞክራሲያዊ ነበሩ። ኢ.ዴሞክራሲዊነታቸው ማንኛውንም የተለየ አመለካከት ያለርህራሄ ለማጥፋት እንዲወስኑ አድርጓቸዋል። ይህ ደግሞ በስርአት ደረጃ ይፋ የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚፈጸምበትን ሁኔታ ፈጥሯል። ይህ የሰብአዊ መብት ጥሰት በአዋጅ የተፈጸመበት ሁኔታም ነበር። ሰዎች የተለየ አመለካከት በመያዛቸው፣ በመግለጻቸው፣ በይፋ ለማራመድ በመሞከራቸው ብቻ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተገርፈዋል፤ ታስረዋል። ለዚህም የቀይ ሽብርን የግድያና የአፈና ዘመቻ ያስታውሷል።

በጊዜ ጎዳና ላይ የኋላ ተጉዤ ያለፉትን ስርአቶች ያስታወስኩት ያለምክንያት አይደለም። እንዳስታውስ የቀሰቀሰኝ ሰሞኑን በገዢው ፓርቲ ኢ.ህአዴግና ህጋዊ ሆነው በሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ.ዎች መካከል ድርድርና ክርክር ለማካሄድ የተጀመረውን ሂደት መነሻ በማድረግ የዚሁ ድርድር አካል በሆኑ፤ እንዲሁም የድርድሩና የክርክሩ ሂደት በአገሪቱ የሚያጸናው ሰላም ያሰጋቸው የአገሪቱ ጠላቶች በተላላኪዎቻቸው አማካኝነት የሚያቀርቧቸው ሃሳቦች ናቸው።

በተለይ የድርድሩና የክርክሩ ተሳታፊ የሆነው ሰማያዊ ፓርቲ አዲሱ ሊቀመንበር አቶ የሺዋስ አሰፋ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ የቅዳሜ የካቲት 11 ዕትም ላይ ***ምርጫ ቦርድ በሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች ውዝግብ ላይ ውሳኔውን አሳወቀ*** በሚል ርዕስ በቀረበው ዜና ላይ በሂደት ላይ ያለውን ድርድርና ክርክር አስመልክተው የሰጡት አስተያየት ወዳለፉት ስርአቶች መልሶኛል። ልተቸውም ወድጃለሁ። ልብ በሉ፤ የማንኛውንም ዜጋ የፈቀደውን አስተያየት የመስጠት የማይገሰስ መብት አከብራለሁ። እናም አስተያየት መስጠታቸውን በራሱ እንደጥፋት አልወሰደውም። ለትችት ያነሳሳኝ የተዛባና አሁን ያለውን የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ የማይወክል ሆኖ ስላገኘሁት ነው። በመሆኑም እኔም እንደማንኛውም ዜጋ አቶ የሺዋስና ሌሎች በተለይ በማህበራዊ ሚዲያና ውጭ አገር ባሉ ሚዲያዎች በተለይ ከድርድሩና ከክርክሩ ጋር በተያያዘ የሰጧቸውን አስተያየቶች ባለኝ ሃሳብን የመግለጽ መብት ተጠቅሜ ልተቸው ወድጃለሁ።

አቶ የሺዋስ ፓርቲያቸው እውነተኛ ድርድር ለማድረግና ሕዝቡ በድርድሩ እምነት እንዲያድርበት በቅድሚያ የፖለቲካና የሀሊና እስረኞችን ይፈቱ፣ የሚል አቋም እንዳለው ገልጸዋል። አያይዘውም፤ የሰማያዊ ፓርቲን ያሀል አባላት የታሰሩበት አንድም ተቃዋሚ ፓርቲ የለም፤ ድርድሩ ከመጀመሩ በፊት ሊፈቱ ይገባል ብለዋል። የፖለቲካ እስረኛ ያሏቸውን ሰዎች መፈታት እንደቅድመ ሁኔታ አቀምጠዋል።

እንግዲህ አቶ የሺዋስ ፖለቲከኛ ናቸው። በኢፌዴሪ ህገመንግስት በተረጋገጠው የአመለካከት ነጻነት፤ የፈቀዱትን አመለካከት የመያዝ፣ በአመለካከት የመደራጀት፣ አመለካከትን በይፋ የማራመድና የመግለጽ፣ ለፖለቲካ ስልጣን የመፎካከር ወዘተ. መብት ተጠቅመው በይፋ የሚንቀሳቀሱ ፖለቲከኛ ናቸው። ለዚያውም የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፤ ፓርቲያቸው ህጋዊ እውቅና አግኝቶ በተንቀሳቀሰባቸው ያለፉት አምስት ዓመታት በህዝብ ውክልና ስልጣን ከተረከበው ኢህአዴግ ፍጹም ተቃራኒ የሆነ አቋማቸውን በይፋ ሲያራምዱ ቆይተዋል። የፓርቲያቸው አቋም የገዢውን ፓርቲ ኢህአዴግን አቋም ብቻ ሳይሆን፤ የኢፌዴሪን ህገመንግስት አንዳንድ ድንጋጌዎችም ይቃወማል። ለምሳሌ፤- ሰማያዊ ፓርቲ ለኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብት ያረጋገጠውን የህገመንግስቱን አንቀጽ 39 በይፋ ይቃወማል። ሰማያዊ ፓርቲ የኢትዮጵያ የአስተዳደር መዋቅር ብሄራዊ ማንነትን ሳይሆን በዘውዳዊው ስርአትና በወታደራዊው ደርግ የስልጣን ዘመን እንደነበረው መልከዐምድርን፤ ወንዝ፣ ተራራ፣ ሸለቆ . . . መሰረት በማድረግ መዋቀር አለበት የሚል አቋም ያለው ፓርቲ ነው። አንዳንዴ አመራሮቹ በሚሰጡት አስተያየት ኢትዮጵያ ውስጥ ብሄር የለም ሲሉም ተደምጧል።

ልብ በሉ፤ ይህ አቋም ህገመንግስቱን፣ በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ አቋምና አሁን ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ የሚኖሩትን ብሄሮችንና ብሄረሰቦችን አቋምና እምነት ይጻረራል። በዚህ ምክንያት ግን አንድም የሰማያዊ ፓርቲ አመራር ወይም አባል አልታሰረም። አቶ የሺዋስም አልታሰሩም። ሰማያዊ ፓርቲ የህገመንግስቱን ምሰሶ የሚጻረር አቋም ስለያዘ እንዳይንቀሳቀስ ታግዶም አያውቅም። ሌሎች ፓርቲዎች፣ የተለየ አመለካከት አራማጅ ቡድኖችና ግለሰቦችም በያዙት፣ በሚያራምዱትና በገለጹት አመለካካት ምክንያት ታግደውና ታስረው አያውቁም። ይህ በተጨባጭ ያለ ከማንም በላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች የሚያወቁት እውነት ነው። አንድ ግለሰብ ወይም የአንድ

ቡድን አባላት የፖለቲካ ወይም የህሊና እስረኛ የሚባሉት በያዙት፣ በሚያራምዱትና በገለጹት አመለካካት ምክንያት ሲታሰሩ ነው። በኢትዮጵያ ይህ ስላልተደረገ የፖለቲካ ወይም የህሊና እስረኛ የለም። እናም *ከኢህአዴግ ጋር ድርድር ለማድረግ በቅድሚያ የፖለቲካ ወይም የህሊና እስረኞች ይፈቱ!* በሚል እንደቅድመ ሁኔታ የቀረበው የሰማያዊ ፓርቲ አቋም መሰረተ ቢስ ነው።

ልብ በሉ፤ በፖለቲከኛነት የሚታወቁ በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ወይም ቅጣት የተወሰነባቸው ፍርደኛ ፖለቲከኞች የሉም እያልኩ አይደለም። እነዚህ ሰዎች የታሰሩት ግን በያዙትና በሚያራመዱት አቋም ምክንያት ሳይሆን፣ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ወይም ከልዩ ባህሪው በመነጨ በህጉ በወንጀልነት የተደነገገን ድርጊት በመፈጸም ተጠርጥረው ወይም መፈጸማቸው በማስረጃ ተረጋግጦ ነው። እነዚህ ደግሞ የፖለቲካ እስረኞች አይደሉም። የወንጀል ተጠርጣሪዎች ወይም አጥፊዎች እንጂ፤

እናም፣ የሰማያዊ ፓርቲ ጥያቄ የአገሪቱን የፖለቲካ ምህዳር ወቅቱ በሚጠይቀው ልክ ማስፋትን ዓላማው በማድረግ ለመካሄድ በዝግጅት ላይ ባለው ድርድር ላይ ለመሳተፍ የወንጀል ተጠርጣሪዎች ወይም ወንጀለኞች ይፈቱ የሚል ቅድመ ሁኔታ ነው ያስቀመጠው፤ ሰማያዊ ፓርቲ የዘነጋው ሌላው ነገር መንግስት ወይም ኢህአዴግ በህግ ከተደነገገው የይቅርታ ስርአት ውጭ ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ ያለና ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦ በፍርድ ቤት ቅጣት የተወሰነባቸውን እስረኞች የመፍታት ህጋዊ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው። ሰማያዊ ፓርቲ ኢህአዴግ በህግ ያልተሰጠውን ተጠርጣሪዎችንና ፍርደኞችን ነጻ የመልቀቅ ተግባር እንዲፈጽም ነው የጠየቀው፤ በፍርድ ቤት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት ወይም የፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻርና መቀየር የአምባገነን መንግስት መገለጫ ነው።

እንግዲህ በጽሁፌ መግቢያ ላይ በጊዜ ጎዳና ወደኋላ ተጉዤ ኢትዮጵያውያን የተለየ አመለካከት ስለያዙ ብቻ ይታሰሩ፣ ይገረፉና ይገደሉ የነበሩባቸውን ስርአቶች እንዳስታወስ ያደረገኝ ይህ የሰማያዊ ፓርቲ አቋም ነው። የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች ወጣቶች ቢሆኑም ስላለፉት ስርአቶች ምንም አያውቁም ማለት ይከብደኛል። እነርሱም*አውቀው ካልረሱት በስተቀር፤*

በኢህአዴግና ህጋዊ ሆነው በሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎቸ መካከል ሊደረግ በሂደት ላይ ያለውን ድርድርና ክርክር መነሻ በማድረግ ሌሎችም አሰተያየቶች ተሰጥተዋል። ከእነዚህ መካከል *ህገመንግስቱ ይቀየር* በሚል የቀረበውን ልመለከተው ወድጃለሁ። እርግጥ ነው የኢፌዴሪ ህገመንግስት አይነኬ መለኮታዊ ሰነድ አይደለም። ወቅቱ በሚጠየቀው ልክ ይሻሻላል። ይህም በህገመንግስቱ ላይ ሰፍሮ እናገኘዋለን፤ በህገመንግስቱ አንቀጽ 104 እና 105 ላይ።

*አንቀጽ* 104 ***የህገመንግስት ማሻሻያ ሃሳብ ስለማመንጨት*** በሚል ርዕስ ስር፤

> *አንድ የህገመንግስት ማሻሻያ ሃሳብ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የደገፈው፣ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የደገፈው ወይም ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ ሶስተኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የደገፉት ከሆነ ለውይይትና ለወሳኔ ለመላው ህዝብና የህገመንግስቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክለሎች ይላካል። ይላል።*

*አንቀጽ* 105 *ደግሞ* ***ህገ መንግስቱን ስለማሻሻል*** በሚል ርዕስ ስር፤

1. *በዚህ ህገመንግስት ምዕራፍ ሶስት የተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች በሙሉ፣ ይህ አንቀጽ እንዲሁም አንቀጽ* 104 *ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፤*
   *ሀ. ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ብልጫ ሲያጸድቁት፤*
   *ለ. የፌደራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶሰተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቀውና፣*
   *ሐ. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ማሻሻያውን ሲያጸድቀው ነው።*

2. *በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ* 1 *ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፤*
   *ሀ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሶሰተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት፣*
   *ለ. ከፌዴሬሽኑ አባል ክልልች ምክር ቤቶች ውስጥ የሁለት ሶስተኛ ክልሎች ምክር ቤቶች በድምጽ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት ነው። ይላል።*

የኢፌዴሪ ህገመንግስት የሚሻሻለው ከላይ በተገለጸው መንገድ ብቻ ነው። ህገመንግስቱን በፓርቲዎች ድርድር ማሻሻል አይቻልም። የህገመንግስቱ ባለቤት የፖለቲካ ፓርቲዎች አይደሉም፤ ህዝብ እንጂ፤ በመሆኑም በገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚደረገው ድርድር አጀንዳ የህገመንግስት ማሻሻያ ሊሆን አይችልም። እርግጥ በዚህ ድርድር የህገመንግስት ማሻሻያ ሃሳቦች ሊመነጩ ይችላሉ። ህገመንግስቱ በዚህ መነሻነት ሊሻሻል የሚችለው ግን ከላይ የተገለጸውን የህገመንግስት ድንጋጌ ተከትሎ ብቻ ነው።

እንግዲህ በኢህአዴግና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ድርድርና ክርክር የሚካሄደው በህገመንግስቱ ማዕቀፍ ውስጥ ነው። ዓላማውም የአገሪቱን የፖለቲካ ምህዳር (ዴሞክራሲ) ወቅቱ በሚጠይቀው ልክ ማስፋትና ማጥለቅ፣ ሁሉም የህዝብ ድምጾች ሊደመጡ የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር አስተማማኝ ሰላም ማስፈን፣ በመሰረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ብሄራዊ መግባባት መፍጠር፤ ወዘተ. ነው። በመሆኑም፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደድርድሩ ሲሄዱ እነዚህን መሰረታዊ ዓላማዎች ማሳካት ቀዳሚ ግባቸው ቢሆን ለአገሪቱና ለህዝቡ መልካም ነው። በህገመንግስታዊ ስርአቱ አኩርፈው ስርአቱን በሃይል ለማፍረስ በውጭ አገራት ያደፈጡና የኢትዮጵያ ጠላቶች የትርምስ ስትራቴጂ አስፈፃሚ የሆኑ ቡድኖች ወደሰላምና የሰፋ የፖለቲካ ምህዳር የሚወስደውን ድርድርና ክርክር ለማደናቀፍ የሚነዙትን ማደናገሪያ ወሬ በጥንቃቄ መመርመር ለህዝብና ለአገር ቆመናል ከሚሉ ህጋዊ ሆነው ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይጠበቃል። ህዝብም ተቆርቋሪ መስለው የሚቀርቡ ቡድኖችና ግለሰቦች የሚነዙትን ወሬ በጥንቃቄ ሊመረምር ይገባል። የተወራ ሁሉ ጠቃሚ አይደለም፤ ያማረ ፍሬ ሁሉ አይበላምና!